# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ሳሙኤል፥የእግዚአ ብሔር ልጅ-ባሪያ



ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest; Alastair Paterson
ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): Lyn Doerksen
የተተረጎመው: Henok Estifanos
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ሐና መልካም ሴት ነበረች፤ሕልቃና የተባለ መልካም ሰው አግብታ ነበር። ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እና ለሌሎች መልካምነትን የሚያሳዩ ነበር።   ነገር ግን በሐና ህይወት ውስጥ አንድ ነገር ጠፍቶ ነበር።ልጅ



ይኖራት ዘንድ ትፈልግ ነበር። ኦ፤እንዴት ልጅ ፈለገች! ለብዙ ጊዜ ትጠብቅ እና ትጸልይ እንዲሁም ተስፋ ታደርግ እና ትጠብቅ ነበር። ምንም ልጅ አልመጣም!



በየዓመቱ፤ሐና ለአምልኮ ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ትወጣ ነበር።በአንዱ ዓመት ላይ እግዚአብሔር ልጅ የሚሰጣት ከሆነ ልጁ ለዘለዓለም የእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆን ዘንድ እንደምትሰጠው ተሳለች።



ሽማግሌው ኤሊ ሐና
ስትጸልይ ተመለከታት።
እርሱም ሐና ሰክራለች
ብሎ አሰበ ምክንያቱም
ከንፈሯ ይንቀሳቀስ እንጂ
የምትናገረው
አይሰማም ነበር።
ኤሊም ሐናን
ገሰጻት!



ነገር ግን ሐና ጸሎቷ ልጅ ለማግኘት እንደሆነ እና ለእግዚአብሔር የተሳለችውን ለኤሊ ነገረችው።"በደኅና ሂጂ" ዔሊም፡- የእስራኤልም አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ ብሎ መለሰላት።" የኤሊም ቃላት ለሐና ተስፋ ሰጣት።

ወዲያው ታላቅ የሆነ ደስታ የሐናን ልብ ሞላው፡፡"እግዚአብሔርም አሰባት" ጸሎቷንም መለሰ፡፡ እሷ እና ሕልቃና ሳሙኤል የተባለ ህጻን አገኙ (ስያሜውም "እግዚአብሔር ሰማኝ" ማለት ነው)፡፡ ነገር ግን ሐና እግዚአብሔርን እና የገባችውን ቃል ታስባለችን?





ሐናም ወደ መቅደስ
በየዓመቱ መሄድ
አቆመች። አ፤ወዳጄ!
ለእግዚአብሔር
የተሳለችውን ስለት
አላከበረችምን?
አይደለም፤ሐና ሳሙኤል
በቤተመቅደስ ውስጥ
መኖር የሚችልበት
እድሜ ላይ እስኪደርስ
እና ኤሊን
በእግዚአብሔር
አገልግሎት ይረዳው
ዘንድ እንዲችል ትጠብቅ
ነበር። ከዚያም ወደ
መቅደስ ይዘው



እግዚአብሔርም
የሐናን ታላቅ የሆነ
ታማኝነት
አከበረ።ከሳሙኤል
በኋላም
እግዚአብሔር ሦስት
ወንዶች ልጆች እና
ሁለት ሴት ልጆችን
ሰጣት።በየዓመቱ፤
ሐና እግዚአብሔርን
ለማምለክ ወደ
እግዚአብሔር
መቅደስ ትወጣ
ነበር-ለሳሙኤል
የሰራችለትን ልብስ
ታመጣለት ነበር።

ሳሙኤል የኤሊ ረዳት ብቻ አልነበረም። አፍኒንና ፊንሐስ በዚያ ያገለግሉ ነበር።ነገር ግን ክፉ የሆኑ ነገሮች እያደረጉ እግዚአብሔርን ያሳዝኑ ነበር፤አባታቸው ኤሊ እንኳን ቢለምናቸው ሊቀየሩ አልቻሉም። ኤሊ በመቅደስ እንዳያገለግሉ ሊያባራቸው ይገባ ነበር።ነገር ግን እርሱ አላደረገውም።





በአንድ ምሽት፤ሳሙኤል አንድ
ድምጽ ሰማ። ግን ትንሹ ልጅ
ኤሊ የጠራው እንደሆነ አሰበ። ኤሊ ዘንድ ሄዶ "አቤት" አለ። ኤሊም "አልጠራሁም" ብሎ መለሰለት።ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ። ኤሊም እግዚአብሔር ሳሙኤልን ሊያናግረው እንደፈለገ አወቀ። ዔሊም ሳሙኤልን፡- ሄደህ ተኛ፤ ቢጠራህም፡- "አቤቱ፥ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው አለው።" ከዚ የም

ጠዋት ሲሆን ኤሊ ሳሙኤልን ጠራው። ሳሙኤልም "እግዚአብሔር የነገረህ ነገር ምንድር ነው?" ብሎ ጠየቀው። ወጣቱ ሳሙኤልም ሁሉንም ነገረው። በጣም አስጨናቂ የሆነ መልዕክት ነበር-እግዚአብሔር ሁሉንም የኤሊን ቤት ሊያጠፋው ነው ምክንያቱም አፍኒንና ፊንሐስ ሐጢአትን ሰርተዋልና።



የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ እውነት ሆነ። ከፈሊስጤም ጋር በነበረው ጦርነት የኤሊ ሁለቱ አመጸኛ ልጆች የእግዚአብሔርን ታቦት በእስራኤል ሰራዊት ፊት እየመሩ ሄዱ። የጠላት ሰራዊትም ታቦቱን ማረከ፤አፍኒንና ፊንሐስ ከበርካታ እስራኤላውያን ጋር ገደላቸው።ኤሊም ይህን በሰማ ጊዜ፤ከወንበሩ ወድቆ፤አንገቱ ተሰብሮ በዚያው ቀን ሞተ።



የእግዚአብሔር ታቦት በፊሊስጤማውያን ላይ ብዙ ችግሮችን አመጣባቸው፡፡በዳጎን ቤት ውስጥ አኖሩት፤ዳጎን የእነርሱ የውሸት አምላክ ነው፡፡በነጋውም፤ዳጎን በአፍጢሙ ተደፋ፡፡ፊሊስጤማውያንም ዳጎኑንን አነሱት-ነገር ግን በሚቀጥለው ጠዋትም እንደገና ወደቀ፡፡በዚህ ጊዜ ዳጎኑ ብዙ ቦታ ላይ ተሰባበረ፡፡





በሽታ እና ሞት
በፊሊስጤማውያን
መካከል
ተዛመተ፡፡እግዚአብሔር
እየቀጣቸው እንደሆነ
ለመመልከት፤የሚያጠቡት
ን ሁለቱን ላሞች፥
በሰረገላም ጠምደው
ከታቦቱ ጋር መውሰድ
ነበረባቸው፡፡ነገር ግን
አንበሶቻቸውን በቤት
ውስጥ
ዘጉባቸው፡፡"ላሞቹን ወደ
እስራኤል ከወሰዷቸው እና
አንበሶቻቸውን
ከተዋቸው፤እግዚአብሔር



እንግዲህ ሳሙኤል አሁን በደንብ ያደገ ሰው ነው፤ለእስራኤል ህዝብም ተናራቸው። "ወደ እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ ከተመለሳችሁ... ፊሊጤማውያንን በእጃቾ ላይ ይጥልላችኋል። "ህዝቡም ታማኝ የሆነውን የእግዚአብሔርን ነብይ ታዘዙ። ሳሙኤል በነበረበት ዘመን የእግዚአብሔር እጅ በፊሊስጤማውያን ላይ ከበደች።

ሳሙኤል፤የእግዚአብሔር ልጅ-ባሪያ

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

1ኛ ሳሙኤል 1-7

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16